# የ፬ኛ ክፍል

## የሙዚቃ ሲለበስ

አዲስ አበባ
2000

## መ ግ ቢ ያ

ይህ የሙዚቃ ሲለበስ በአጠቃላይ 16 ክፍለ ጊዜ ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ሴሚስተር 8 ክፍለ ጊዜ እንዲኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል።

ሲለበሱ የፕሮጀክት መርህ መማርን ( Project – Based Learning ) መሠረት ያደረገ ሲሆን ከዚህ አንፃር ሲለበሱ ውስጥ የሚከተሉትን  መርሆዎች ለማካተት ተሞክሯል።

- ከተግባር ጋር የተያያዙ የመማር ስልቶች ፣
- ሁሉም ተማሪዎች ለመማር ዕድል መስጠት፣
- ተማሪዎች ለመማር ራሳቸው ኃላፊነት የሚወስዱበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረግ፣
- ፕሮጀክቶች ትርጉም ያለው መማርንና ከተማሪዎች ቀደሞ ልምድ ጋር የተገናዘቡ መሆናቸው፣
- የመማር ማስተማሩ ሂደቱና ፕሮጀክቶች በተማሪዎች እንዲገመገሙ መደረጉ፣
- እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ሥራ እንዲገመግም የሚያበረታታ መሆኑ፣
- ተማሪዎች የጠለቀ ግንዛቤ እንዲያገኙ ዕድል መሰጠቱ፣
- መምህሩ ትምህርቱን በማመቻቸትና አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ማተኮሩ።

ስለዚህ እነዚህን ዋና ዋና መርሆዎች መሠረት በማድረግ ትምህርቱን መተግበር ከመምህሩ ይጠበቃል።

## ክፍለ ትምህርት 1 ፡ የሙዚቃ ጠቀሜታና ክፍሎች /2 ክፍለ ጊዜ/

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የሙዚቃን ጠቀሜታ ከሰሙት ዜማዎች አንፃር በመተንተን በሪፖርት ያጠናቅራሉ።
- የተለያዩ ዘፋኞችን ዜማዎችና የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለዛ ተንትነው ያቀርባሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o የተለያዩ ዜማዎችን በማድመጥ ሙዚቃ ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝረው በመፃፍ ያቀርባሉ። | 1.1. የሙዚቃ ጠቀሜታ<br>/1 ክ/ጊዜ/ | **ክንዋኔ 1**<br>o የተለያዩ ሙዚቃዎችን በማድመጥ ምን ስሜት እንደሚሰማቸው እያንዳንዱ ተማሪ በዝርዝር በመፃፍ ሪፖርት ማቅረብ ።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ሪፖርቱን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡና ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ። |
| o ከ3 ያላነሱ የተለያዩ ዘፋኞችን ዜማዎች ለዛ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን በመተንተን ሪፖርት ያቀርባሉ፡<br>o ከ3 ያላነሱ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለዛ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ተንትነው ሪፖርት ያጠናቅራሉ። | 1.2. የሙዚቃ ክፍሎች<br>/1 ክ/ጊዜ/<br><br>1.2.1. የድምፅ ለዛ<br>o የሰው ድምፅ<br>o የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>1.2.2. ሀርሞኒ | **ክንዋኔ 1**<br>o ከ3 ያላነሱ ዮተለያዩ ዘፋኞችን ዜማዎች ለዛና ሀርሞኒ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን በመተንተን በሪፖርት መልክ ማጠናቀር።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ያቀናበሩትን ለክፍሉ ተማሪዎች ማቅረብና ልምዳቸውን ማካፈል።<br>**ክንዋኔ 3**<br>o የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለዛ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ተንትነው በሪፖርት መልክ ማጠናቀር። |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣**

- ካሴቶች፣ካሴት ቴፕሪከርደር

**ክትትልና ግምገማ**

- ሙዚቃ ያለውን ጠቀሜታ ካዳመጡት ሙዚቃ አንፃር መተንተናቸውን ሪፖርታቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፣
- የተለያዩ ዘፋኞችን ዜማዎችንና የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለዛ መተንተናቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 2 ፡ የሙዚቃ ኖታዎች ምልክቶችና አጨዋወታቸው /3 ክፍለ ጊዜ/

- ቀላል ሪትሞችን ጭብጨባና የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በመጫወት ያሳያሉ።
- የሙዚቃ ፍጥነት /ቴንፓ/ና የሙዚቃ መጠን /ዳይናሚክስ/አይነቶች  አተገባበር ቀላል ሪትምን በመጫወት ያሳያሉ።
- የድብልቅ ጊዜ አመልካቾችን ቀላል ሪትሞችን በመጫወት ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ቀላል ነጥብ ያላቸውንና የሌላቸውን ከትሪፕሌትና ሲንኮፔሽን ጋር ተቀላቅለው የተዘጋጁ ሪትሞችን በጭብጨባ ወይም በምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በመጨዋት ያሳያሉ። | 2.1. የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸው ኖታዎች<br>/ ክ/ጊዜ/<br>2.1.1. ትሪፕሌት<br>2.1.2. ሲንኮፔሽን<br>2.1.3. ባለነጥብ ኖታዎች<br>o አንድ ስምንተኛ | o ስለኖታዎቹ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ ክንዋኔውን እንዲሰሩ ማድረግ።<br>**ክንዋኔ 1**<br>o ከ20 ያላነሱ ቀላል ነጥብ ያላቸውንና የሌላቸውን ከትሪፕሌትና ከሲንኮፔሽን ጋር በማቀላቀል በጭብጨባ ወይም በከበሮ መጫወት። |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| <br><br><br><br>o የድብልቅ የጊዜ አመልካቾችን ፅንሰ ሀሳብ ተረድተው ቀላል ምቶችን በመጫወት ያሳያሉ።<br>o የሙዚቃ ፍጥነት /ቴንፓ/ አይነቶችና ተግባር ተገንዝበው ቀላል ሪትሞችን በመጫወት ያሳያሉ።<br><br><br><br><br><br>o የሙዚቃ መጠን /ዳይናሚክስ/ አይነቶችና ተግባር ተገንዝበው ሪትሞችን በመጫወት ያሳያሉ። | <br><br><br><br>2.2. ሪትምና ሜትር /1ክ/ጊዜ/<br>2.2.1. ድብልቅ (compound)<br>o 6 : 9<br>o 8 : 8<br>2.3. የሙዚቃ ፍጥነት /ቴምፓ/<br>o Adjo (በጣም አነስተኛ)<br>o Andante (ዝግተኛ)<br>o Moderato (መሐከለኛ)<br>o Allegro (ፈጣን)<br>o Presto (በጣም ፈጣን)<br><br>2.4. የሙዚቃ መጠን /ዳይናሚክስ / /1ክ/ጊዜ/<br>o PP (Pianossimo ) በጣም ለስላሳ ያልጮኸ | ምሳሌ፡<br>ሀ/<br>ለ/<br>ሐ/<br><br><br>**ክንዋኔ 1**<br>o ከ5 ያላነሱ በድብልቅ የተዘጋጁ ሪትሞችን በጭብጨባ ወይም በከበሮ መጫወት።<br>ምሳሌ፡<br>ሀ/<br><br><br><br><br>**ክንዋኔ 2**<br>o በተለያዩ የጊዜ አመልካቾች የተዘጋጁ ሪትሞችን በጊዜ ፍጥነት መሠረት መጫወት ፡ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | o P (Piano ) ለስላሳ<br>o ( Fortissimo ) በጣም የጮኸ<br>o (Forte) የጮኸ<br>o > Decrescendo<br>o < Crescendo<br>o • Staccato<br>o < Stress | ምሳሌ፡<br>ሀ/<br>ለ/<br>ሐ/ |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች**

- o ምልክቶቹን የያዙ ቻርቶች፣
- o ከምልክቶቹ ጋር የተያያዙ ዜማዎች፣
- o ካሴት ፡ ካሴት ሪከርደር፣

**ክትትልና ግምገማ**

- o ሪትሞቹን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ፣
- o የድብልቅ ጊዜ አመልካቾችን የሙዚቃ ፍጥነት /ቴንፓ/ና የሙዚቃ መጠን /ዳይናሚክስ/ መገንዘባቸውንና በተግባር ማሳየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 3 ፡ የሙዚቃ አፃፃፍና አዘማመር /3 ክፍለ ጊዜ/

- o የሜጀርና ማይነር ስኬሎችን በመገንዘብ ሕጉን ተከትለው በመደርደር ያሳያሉ።
- o የሜጀርና ማይነር ስኬሎችን እንዲሁም ኦክታቭን በመጠኑ በመዘመር ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| o የቶናሊቲን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ።<br>o የሜጀርና ማይነር ስኬሎችን ልዩነትና አንድነት ይለያሉ።<br>o ቢያንስ የሁለት ሜጀርና የሁለት ማይነር ስኬሎችን አደራደር ሰርተው ያሳያሉ።<br>o ቢያንስ የአንድ ሜጀርና ማይነር ስኬሎችን ይዘምራሉ። | 3.1. የሙዚቃ ድምጾች አደረጃጀት /ቁልፎችና ስኬሎች/ /3 ክ/ጊዜ/<br>3.1.1. ቶናሊቲ<br>3.1.2. ኦክታቭ<br>3.1.3. ሜጀር ስኬል<br>3.1.4. ማይነር ስኬል | o ፅንሰ ሀሳቦቹን ተማሪዎች በሚገባቸው መንገድ ማስረዳትና ክንዋኔዎቹን እንዲሰሩ ማድረግ።<br>**ክንዋኔ 1**<br>o የተለያዩ ድምጾችን በመውሰድ በኦክታቫቸው መሠረት ድምፅ ማውጣት።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o የሜጀር ስኬሎችንና ማይነር ስኬሎችን ሕግን ተከትለው መደርደር ቢያንስ በሲ ሜጀር እንዲሁም በኤ ማይነር ስኬሎቹን በመወጣትና በመውረድ መዘመር /መለማመድ/።<br>o የተለማመዱትን ለክፍላቸው ተማሪዎች ማሳየት |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡**

- o የሜጀርና ማይነር ስኬሎች ቻርት፣
- o ከሁለት ኦክታቭ ያላነሰ ውድ ያልሆነ ኪ ቦርድ ፣

**ክትትልና ግምገማ**

- o የቶናሊቲንና የስኬሎችን ፅንሰ ሀሳብ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣

- የስኬሎችን አደራደር መስራታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ሜጀርና ማይነር ስኬሎችን መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 4 ፡ ባህላዊ ዘፈኖች /3 ክፍለ ጊዜ/

- በክልሉ የሚገኙ ከጀግንነት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን በመተንተን ሪፖርት ያቀርባሉ።
- ከጀግንነት ጋር የተያያዙ ሁለት ባህላዊ ዘፈኖችንና በአምባሰል የተዘፈኑ ሁለት ዜማዎችን በመጫወት ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ከጀግንነት ጋር የተያያዙ በክልሉ የሚገኙ ባህላዊ ዘፈኖችን ተንትነው በሪፖርት መልክ ያቀርባሉ።<br>o ቢያንስ ሁለት የጀግንነት ባህላዊ ዘፈኖችን በመጫወት ያሳያሉ።<br>o ቢያንስ ሁለት በአምባሰል ቅኝት ዜማዎችን በማዜም ያሳያሉ። | 4.1. ከጀግነት ጋር የተያያዙ በክልሉ የሚገኙ ባህላዊ ዘፈኖች፣ /2 ክ/ጊዜ/<br><br>4.2. በአምባሰል ቅኝት የተዘፈኑ ዜማዎች፣ /1 ክ/ጊዜ/ | **ክንዋኔ 1**<br>o በክልሉ የሚገኙ ከ2-3 የሚደርሱ ከጀግንነት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን ፣ ግጥም ፣ አልባሳት ፡ ዘፈኖቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ አጨዋወት በመዘርዘር በሪፖርት መልክ ማቅረብ፡<br>o ሪፖርቱን ለተማሪዎቹ ማቅረብና አስተያየት መቀበል፣<br>o መጫወት የተሻለውን ተማሪዎች እንዲመርጡ ማድረግ፣<br>**ክንዋኔ 2**<br>o የተመረጡትን ባህላዊ ዘፈኖች በቡድን ተለማምደው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣በቀረበው አጨዋወት |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | ላይ ተማሪዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣ |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡**

- ካሴት ፣ ካሴት ሪከርደር ፣
- ለጀግንነት ባህላዊ ዘፈኖች የሚያስፈልጉ አልባሳት ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሰፈላጊ ቁሳቁሶች፣

**ክትትልና ግምገማ**

- ባህላዊ ዘፈኖችን መተንተናቸውን ሪፖርታቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፣
- ባህላዊ ዘፈኖቹንና ዜማዎቹን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 5 ፡ መዝሙሮች /3 ክፍለ ጊዜ/

- ከ4 ያላነሱ ጠቀሜታ ያላቸውን መዝሙሮች ግጥምና ዜማ ይደርሳሉ።
- የተደረሱትን መዝሙሮችና ሌሎች ዜማዎችን በመዘመር ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ከቤተሰብ ምጣኔ ፡ ከተፈጥሮ ውበት ፡ ከሰላም፡ ከባህልና ቅርስ መጠበቅ ፡ ከመልካም ሥነምግባር ጋር የተያያዙ ቀላል መዝሙሮችን ይደርሳሉ።<br>o ከደረሷቸው መዝሙሮች ውስጥ የተመረጡትንና ካልደረሷቸው ውስጥ ታዋቂ ዜማዎችን በመዘመር ያሳያሉ። | 5.1. ከቤተሰብ ምጣኔ፣ ከተፈጥሮ ውበት ፣ ከሰላም ከባህልና ቅርስ መጠበቅ፣ ከመልካም ሥነምግባር ጋር የተያያዙ መዝሙሮች፣<br>/3 ክ/ጊዜ/<br>5.1.1. ግጥም መድረስ<br>5.1.2. ዜማ መድረስ<br>5.1.3. መዘመር | **ክንዋኔ 1**<br>o በርዕሶቹ ላይ ግጥም በጥንድ ሆነው መድረስ፣<br>o ከተደረሱት ውስጥ የተሻለውን ተማሪዎቹ እንዲመርጡ ማድረግ፣<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ለተመረጡት ግጥሞች በቡድን ሆነው ዜማ ማውጣት፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | o ከወጡት ዜማዎች ውስጥ የተሻለውን መምረጥ፣<br>**ክንዋኔ** 3<br>o ከእነዚህ ርዕሶች ጋር የተያያዙ የሚዜሙ ዜማዎችን በመምረጥ ማዜም። |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡**

- o ካሴት ፣ ካሴት ቴፕሪከርደር ፣

## ክትትልና ግምገማ

- o የመዝሙሮቹን ግጥምና ዜማ መድረሳቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ፣
- o መዝሙሮቹንና የመረጧቸውን ሌሎች ዜማዎች ማዜማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

## ክፍለ ትምህርት 6 ፡ የሙዚቃ ታሪክ /3 ክፍለ ጊዜ/

- o ከአፍሪካና አለም አቀፍ ጥቂት ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ፡ ዘፋኞችና ሙዚቃ አቀናባሪዎችን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች አጠናቅረው ያቀርባሉ።
- o የታዋቂ የአፍሪካና አለም አቀፍ ዘፋኞችን ዜማዎች በማዜም ያሳያሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| o ከአፍሪካ ታዋቂ ደራሲያን አቀናባሪዎችና ዘፋኞችን ቢያንስ ከእያንዳንዳቸው የአንዱን አጠናቅረው ያቀርባሉ።<br>o ከአለም አቀፍ ታዋቂ ደራሲያን ፡ አቀናባሪያንና ዘፋኞችን ከእያንዳንዳቸው | 6.1. ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች፣ /3 ክ/ጊዜ/<br>6.1.1. አፍሪካ አቀፍ<br>6.1.2. አለም አቀፍ | **ክንዋኔ** 1<br>o ከአፍሪካ ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያን ቢያንስ የሁለቱን ፣ ከአለም አቀፍ ቢያንስ የሁለቱን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች በሪፖርት መልክ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| የአንዱን አጠናቅረው ያቀርባሉ።<br>o የታዋቂ የአፍሪካና አለም አቀፍ ዘፋኞችን ከእያንዳንዳቸው ቢያንስ አንድ ዜማ በማዜም ያሳያሉ። | 6.2. ታዋቂ ዘፋኞችንና ሙዚቃ አቀናባሪዎች፣<br><br>/1 ክ/ጊዜ/<br><br>6.2.1 አፍሪካ አቀፍ<br>6.2.2 አለም አቀፍ | ማጠናቀር፣ ሪፖርቱን ለክፍሉ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ።<br>**ክንዋኔ 2**<br>o ከአፍሪካ ታዋቂ ዘፋኞች ቢያንስ የሁለቱን፣ ከአለም አቀፍ ቢያንስ የሶስቱን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች በሪፖርት መልክ ማጠናቀር፣ ሪፖርቱን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ አስተያየት መቀበል።<br>ክንዋኔ 3<br>o ከአፍሪካና ከአለም አቀፍ ከእያንዳንዳቸው ቢያንስ የአንድ ታዋቂ ዘፋኝን በመለማመድ ማዜም፣ የተለማመዱትን ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ። |

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡**

o ካሴት ፣ ካሴት ቴፕሪከርደር ፣

**ክትትልና ግምገማ**

- የሙዚቃ ደራሲያን፡ አቀናባሪያንና ዘፋኞች አጠናቅረው ማቅረባቸውን ሪፖርታቸውን በመመልከት /በማንበብ ማረጋገጥ፣
- የታዋቂ ዘፋኞችን ዜማዎች ማዜማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣